# ኢትዮጵያ የአውራ ፓርቲ ወይስ የአሃዳዊ ፓርቲ መገለጫ ስርዓት?

(ክፍል ሁለት)

ከፀሐዬ ደባልቀው
ዋሽንግተን ዲ.ሲ.
February 17, 2012

እስቲ ደግሞ በአንፃሩ የአሃዳዊ ፓርቲ ክስተትና መገለጫ ባህሪውን ለአፍታ እንመልከት፡፡ በተለምዶ በእንግሊዝኛው አባባል (Single Party State) በመባል የሚታወቀው በታሪክ መታየት የጀመረው የቀድሞ የሶቭዬት ሕብረት መንግስት ሥልጣን ላይ በወጣበትና በወቅቱ የፖለቲካ አደረጃጀት ዓይነተኛ መታወቂያ በነበረው በፈላጭ ቆራጩ የፓርቲ ሥልጣን ቁንጮ በሆነው የኮሙዩኒስት ፓርቲ መሰላልነት ነበር፡፡

የአሃዳዊ ፓርቲ በመሠረቱ ከአውራ ፓርቲ የሚለየው ባህርይ የፈላጭ ቆራጭ ፓርቲ መሰረት በሆነው ሕገ መንግስት በማያሻማ መልኩ የስርዓቱ ገዥ ፓርቲ የኮማዩኒስት ፓርቲ ብቻ ነው ብሎ ስለሚደነግግ ብቻ ሳይሆን ሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች በተቀናቃኝነት እንዲደራጁ የማይፈቅድ በመሆኑ እና በግለሰብ ደረጃም ማንም ከገዥው ፓርቲ ውክልና ውጭ ለውድድር መቅረብ የማይቻለው መሆኑንም ጭምር ነው በዓለማችን በታሪክ ከተከሰቱትና ህልውናቸው እስከአሁን ድረስ ከዘለቀው ፈላጭ ቆራጭ የአሃዳዊ ፓርቲዎች መካከል የሚከተሉትን መጠቃቀስ ይቻላል፡፡

አሁን በሥልጣን ካሉት መካከል የኩባ ኮሙዩኒስት ፓርቲ፣ የኮሪያ ሰራተኞች ፓርቲ /ሰሜን ከሪያ/ የሱርያ ባዝ ፓርቲ፣ የኤርትራው ሕዝባዊ ግንባር ለዲሞክራሲና ለፍትህ እና የቬትናም ኮሙዩኒስት ፓርቲ በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳሉ፡፡

በቀሪው ዓለምም አውራ ፓርቲዎች በአጭር ጊዜ የተቋጨ ወይንም ለረዥም ጊዜ የዘለቀ የሥልጣን ዘመን ያስቆጠሩ እንዳሉ ማስተዋል ይቻላል፡፡ በአህጉራችን በአፍሪቃ፣

- የአንጎላው «The Popular Front for the Liberation of Angola"

  ከ1975 እስከ አሁን ድረስ፣
- የቦትስዋናው Botswana Democratic Party

  ከ1966 እስከ አሁን ድረስ፣
- የናይጄሪያው Peoples Democratic Party

  ከ1999 ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ
- የታንዛኒያው Chamacha Mapundize Party

  ከ1964 ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ፣

እንዲሁም

- የደቡብ አፍሪካው African National Congress

  ከ1994 ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ፣

**ከእስያ፣**

- የጃፓኑ Liberal Democratic Party

  1955 - 1993
- የሲንጋፖሩ People's Action Party

  ከ1959 ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ፣
- የህንዱ Indian National Congress

  ከ1947- 1977 ድረስ፣

**ከአውሮፓ**

- የሉክስዘምበርጉ The Christian Social People's Party

  ከ1919 ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ፣

- የስዊዲኑ Swedish Social Democratic Party
  ከ1932 - 1976
- የኖርዌዩ Norwegian Labor Party
  1874 - 1916

<u>በአሜሪካ ግዛቶች፣</u>

- የሜክስኮው፣ Revolutionary Institutional Party
  1920 - 2000
- የአርጀንቲናው National Autonomist Party
  1874 -1916

እንግዲህ ከፍ ሲል ለአብነት የተጠቃቀሱት ሃገሮች ላይ በአንዱ ወይም በሌላው ወቅት ስልጣን ላይ የወጡት አውራ ፓርቲዎች በየሀገሩ ባለው የፖለቲካ ምህዳር ሕገ መንግስታዊ ዕውቅናና ጥበቃ በተቸራቸው አያሌ የፖለቲካ ድርጅቶች መካከል በየጊዜው በተደረገ የፖለቲካ ውድድር የምልዓቱ መራጩን ልብ ያማለሉ፣ የገቡትን ቃል በተግባር የተረጎሙና የሀገርና የወገን ተለዋዋጭ ፍላጎትን ታሳቢ በማድረግ ዓላማቸውን እየቀየሱ በእያንዳንዱ ማዕድና ቤት የሚታይ፣ የሚዳሰስና ሕዝቡን ተጠቃሚ የሚያደርግ ተከታታይና ቀጣይነት ያለው ለውጥ በማስመዝገባቸው እንደሆነ ልብ ይሏል።

በአውራ ፓርቲና በፈላጭ ቆራጩ አሃዳዊ ፓርቲ መካከል ያለውን ሁነኛ ልዩነትና የአቋምና የእምነት አይነፃፀሬነትን ካስተዋልን ጽሁፌን ለመቋጨት ያህል የበለፀጉት አገሮችን ምሳሌ በመጠቃቀስ ልሰናበታችሁ።

በዓለም የዲሞክራሲያዊ ፖለቲካ ተምሳሌት ሆና በምትቀርበዋ አሜሪካ ሁሉም እንደሚያውቀው ሁለት ዋና ዋና ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ማለትም የሪፓብሊካንና የዲሞክራቲክ ፓርቲ ትኬት የያዙ እጩዎች ሥልጣኑን በመፈራረቅ ሲቆጣጠሩት፣ ቢረዝም አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ከስምንት ዓመት በላይ ኘሬዚዳንቱን ሥልጣን ላይ ማቆየት አይችልም የሚል ሕገ መንግስታዊ ማዕቀብ ቢኖርም አልፎ አልፎ ለ12 ዓመታት ያህል በልዩ ሁኔታ የመሩ የአሜሪካ ኘሬዚዳንቶች እንደነበሩ ታሪክ ያስታውሰናል፡፡

ይሁንናም ይህ የፖለቲካ ስርዓቱ መገለጫ የሆነው በሀገር አቀፉ ደረጃ የሁለቱ ዋና ዋና ፓርቲዎች መፈራረቅ እውነት ቢሆንም ከሀገር አቀፍ በተዋረድ አያሌ ትናንሽ የፖለቲካ ፓርቲዎች መኖራቸው ደግሞ ሌላው ሀቅ ነው፡፡ ምነው ቢሉ ዲሞክራሲያዊው የአሜሪካ ሕገ መንግስት ብዙሀን ፓርቲዎች የሚፎካከርበት ስርዓት የዘረጋ በመሆኑ ነው፡፡

በሌላ በኩልም የሪፓብሊካን ይሁን የዲሞክራቲክ ፓርቲ ከሀገር አቀፍ ደረጃ ዝቅ ባሉ የመስተዳደር እርከኖች የዚህኛው ወይንም የዚያኛው ፓርቲ በገዥነት ረዘም ላለ ዘመን የቆዩበት አጋጣሚ መጠቃቀስ ብቻ ሳይሆን በነዚህ ዘመናት ውስጥ ግልፅና ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የምረጡኝ ውድድር በሚካሄድበት አግባብም ቢሆን አልፎ አልፎ በየዕርከኑ የአውራ ፓርቲ ገዥነት ባህርይ ይስተዋላል፡፡

ለአብነት ያህልም የአሜሪካ መናገሻ መዲና የሆነችው የDistrict of Columbia, Washington DC ከንቲባ ከ1973 ዓ.ም. እስከ አሁኑ የከተማዋ ከንቲባ ድረስ በተከታታይ በትረ ሥልጣኑን የጨበጠው የዲሞክራቲክ ፓርቲ እጩ ሆኖ የቀረበው ተመራጭ ሲሆን ከተማዋንም ከተጠቀሰው ወቅት ወዲህ እያስተዳደረ ያለው የዲሞክራቲክ ፓርቲው ነው፡፡

ይህ ባህርይው የዲሞክራቲክ ፓርቲ በተከታታይ ተፎካካሪውን የሪፐብሊካኑን ፓርቲና ሌሎች አናሳ ፓርቲዎችን በመርታት ስልጣኑን በአውራ ፓርቲነት ተቆጣጥሯል ማለት እንደሆነ በሚገባ ይመሰክራል።

ይሽንን እውነታ ስናይ የዲሞክራቲክ ፓርቲው የዋሽንግተን ዲሲን የሥልጣን ወርቃማ ቁልፍ በእጁ በማስገባቱ ከተማዋን የአሃዳዊ ፈለጭ ቆራጭ ፓርቲ ስልጣን መገለጫ ሊያደርጋት ከቶ አይቻልም። ምክንያቱም ዲሞክራቲክ ፓርቲው በአሜሪካ ሕገ መንግስት ብቸኛ ፓርቲ ተብሎ የተቀመጠ ሳይሆን ይልቁንም የአሜሪካው ሕገ መንግስት ማናቸውም ሕጋዊ፣ ሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ ውድድርን የሚከተል አደረጃጀት የሚፈቅድ በመሆኑ የህዝቡን ይሁንታ ያተረፈ ፓርቲ ብቻ የሚዘልቅበት አግባብ መኖሩን ያረጋግጣል።

በአሜሪካ ደቡባዊ የመካከለኛው ግዛት የምትገኘዋ የታላቋ Chicago ከተማም ከ1927 ጀምሮ የዲሞክራቲክ ፓርቲው በእጩነት ባቀረበው ከንቲባ እስከ አሁን ድረስ እየተዳደረች ትገኛለች። መጣጥፌን ለመደምደምም ሌሎች በዲሞክራቲክ ሕገ መንግስት በሚተዳደሩና ግልፅ ሰላማዊ፣ ህጋዊና ዲሞክራሲያዊ ውድድር በሚፈቅዱ አገሮች የሚታየውን የአውራ ፓርቲ ገዥነት ለአብነት ላሳይ፣

የካናዳዋ ግዛት Alberta ከ1971 ጀምሮ በProgressive Conservative Party እየተዳደረች ነው። በካናዳም ይሁን በአሜሪካ የአውራ ፓርቲ በሀገር አቀፉ ደረጃ ለረዥም ጊዜ ሥልጣን ጨብጦ ማየት የተለመደ አይደለም። በአውስትራሊያ ሌላዋ ዲሞክራቲክ አገር የሆነችው የQueensland State ከ1987 ጀምሮ በLabor Party አውራ ፓርቲነት እየተዳደረች ቀጥላለች።

ለማጠቃለልም የቁምነገሩ ዳራ ያለው በአንድ ሀገር የአውራ ፓርቲ መኖር ወይንም አለመኖር የሚወሰነው በዛች ሃገር ሥራ ላይ የዋለው ሕገ መንግስት ዲሞክራሰያዊ መሆንና ይህ ዲሞክራሲያዊ ሕገ መንግስት የብዝሃ ፓርቲ ሕልውና (multi-party setting) መፍቀዱ፣ በሕጋዊ መንገድ የተመዘገበና ሰላማዊ፣ ሕጋዊና ዲሞክራሲያዊ የሆነ ሂደትን አሜን ብለው በመቀበል በሕጉ መንፈስ ሥጋና ቀለም ለመወዳደር ራሳቸውን ያዘጋጁ ፓርቲዎች በአግባቡ እንዲንቀሳቀሱ ሕጋዊ ዕውቅናን የሚሰጥና በአጠቃላይ በየጊዜው በተዋረድ በሚካሄድ ምርጫ ውስጥ ሕብረተሰቡ በሕግ የበላይ ዕውቅናና ጥበቃ ተችሮት ሕገ መንግስታዊ መብቱንና ግዴታውን መወጣቱ ላይ ነው::

በቸር ይግጠመን!!